## ማውጫ

አርዕስት ገፅ

መግቢያ.......................................................................................................1
አስተዋጽኦና ቅኝት ........................................................................................2
ጥናት1: የነህምያ ሃዘን እና ጸሎት..................................................................3
ጥናት 2: የነህምያ የፈረሰውን ቅጥር ጉብኝት.........................................................4
ጥናት 3: የቅጥሩ ሠራተኞች ስብስብ...................................................................5
ጥናት 4: በቅጥሩ ስራ ላይ ውጫዊ ተግዳሮት ......................................................6
ጥናት 5: በቅጥሩ ስራ ላይ ውስጣዊ ተግዳሮት ......................................................7
ጥናት 6: የቅጥሩ እድሳት መጠናቀቅ................................................................ 8
ጥናት 7: ቅጥሩን በንቃት መጠበቅ ...................................................................9
ጥናት 8: የሕጉ መጽሐፍ መነበብ ..................................................................... 10
ጥናት 9: ስለ በደል ጥልቅ ንስሓ.......................................................................11
ጥናት 10: የእግዚአብሔር ምሕረት ባለጠግነት .................................................... .12
ጥናት 11: እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የተደረገ ውል ............................................... 13
ጥናት 12: አዲሶቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች..................................................14
ጥናት 13: የመጡት ካህናትና ሌዋውያን..................................................15
ጥናት 14: የቅጥሩ ምረቃ በዓል.......................................................................  ....16
ጥናት 15: የመጨረሻው የነህምያ የተሃድሶ እርምጃ...................................17

## መግቢያ

### ታሪካዊ ዳራ

የነህምያ መጽሐፍ የአይሁድ ምርኮኞች ከባቢሎንና ከፋርስ ምርኮ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በተፈቀደላቸው ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ስለሚገልጽ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ማጠቃለያ ተደርጎ ይወሰዳል። ከመጽሐፈ ዕዝራ አንድ ወጥ ሆነው በተጻፉበት በዕብራይስጡ የብሎይ ኪዳን መጽሐፍ በሦስት የተደረገውን የምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስን ታሪክ ይዞአል ። ዕዝራ ከመጀመሪያዎቹ ከሁለቱ የመመለስ ጊዜዎች ጋር የትያያዙትን ታሪኮች ሲጽፍ(538 ዓ.ቅ.ክ፣457 ዓ.ቅ.ክ )፣ ነህምያ ደግሞ በሦስተኛው የመመለስ ጊዜ የተፈጸመውን ታሪክ ጽፎአል (444 ዓቅክ) ። በመጽሐፈ ዕዝራ ትኩረት የተደረገበት ቤተ መቅደሱን እንደገና የመሥራት ጉዳይ ሲሆን በመጽሐፈ ነህምያ ደግሞ ትኩረት የተደረገበት የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና የመሥራት ጉዳይ ነበር ። ሁለቱም መጻሐፍት የመንፈሳዊ ተሐድሶን እንዲሁም ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ የመሆንን አስፈላጊነት በአጽንኦት ይገልጻሉ ።

በዕዝራ ዘመን የነበረው ነህምያ ከባቢሎና ከፋርስ ወደ ይሁዳ የተመለሱት ምርኮኞች በችግር ላይ የመሆናቸውን እንዲሁም የኢየሩሳሌም ቅጥር የመፈራረሱን ወሬ በሰማበት ጊዜ የፋርስ ንጉስ የአርጤክስስ ቀዳማዊ የወይን ጠጅ አሳላፊ ነበር ። ስለ ኢየሩሳሌም ችግር ከጸለየ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅጥሩን እንዲሠራ ይፈቀድለት ዘንድ ለንጉሱ ጥያቄ አቀረበ ። ንጉሱም አርጤክስስ ነህምያ የኢየሩሳሌም አገረ ገዥ እንዲሆንና ሄዶም የከተማይቱን ቅጥሮች እንደገና እንዲሰራ ፈቀደለት ። ነህምያ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሳ መሪ እንደመሆኑ ቅጥሩን እንደገና ለመሥራት የአገሩን ሰዎች በማስተባበር አሰባሰበ ። ምንም እንኳ ቅጥሩ እንዲሰራ በማይፈልጉ የእስራኤል ጠላቶች ጠንካራ ተቃውሞ በተደጋጋሚ ቢገጥመውም የቅጥሩን ሥራ በ52 ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሊያጠናቅቅ ቻለ ።ለዐሥራ ሁለት ዓመት የኢየሩሳሌም አገረ ገዥ በመሆን አገለገለ። ለጥቂት ጊዜ ወደ ፋርስ ከተመለሰ በኋላም ለሁለተኛ ጊዜ የይሁዳ አገረ ገዥ በመሆን አገለገለ (ነህ 2:113:6-7) ።

**የነህምያ መጽሐፍ ጸሐፊ** :

ወደ አገራቸው በተመለሱ ትሩፋን/ቅሬታዎች/ መካከል መንፈሳዊ መነቃቃትና ተሐድሶ ይመጣ ዘንድ ነህምያ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ጸሐፊውና ካህኑ ዕዝራ ከፍተኛ እገዛ ያደርግ ነበር። ዕዝራ ይህን መጽሐፍ ሲጽፍም ምናልባትም ነህምያ ሳያግዘው አይቀርም ። ስለዚህ የነህምያ መጽሐፍ ጸሐፊዎች ዕዝራና ነህምያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ሲገመት የተጻፈበት ዘመን ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ430-420 ዓ.ዓ ገደማ ነው።

### የመጽሐፉ ዋና ዓላማና ሐሳብ

የነህምያ መጽሐፍ ዋና ሐሳብ የኢየሩሳሌምን ቅጥር **<u>እንደገና መሥራት</u>** ላይ የሚያውጠነጥን ሲሆን የመጽሐፉ ዓላማ ደግሞ : **(1)** በዕዝራ መጽሐፍ የተጀመረውን የድኅረ ምርኮ ታሪክ ለማጠቃለልና **(2)** በድኅረ ምርኮ የመመለስ ታሪክ በሦስተኛው የምርኮኞች መመለስ ጊዜ እግዚአብሔር በዕዝራና በነህምያ መንፈሳዊ መሪነት ለትሩፋኑ ያደረገውን ለማሳየት ነው።

**አስተዋጽኦና ቅኝት**

የነህምያ መጽሐፍ በሚከተሉት ሦስት ዐበይት ክፍሎች የተዋቀረ ነው።

**I. በነህምያ መሪነት የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና መሥራት:**

**(ከምዕ1:1-7:73):** በዚህ ክፍል የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና ለመስራት ነህምያ አገረ ገዥ የሕዝብ መሪ ሆኖ ያደረገው ነገር ተጠቅሶአል ። ምዕ 1 ነህምያ የቱን ያህል የጸሎት ሰው እንደሆነ በመግለጽ ያለውን መንፈሳዊ ጥንልቀት ያሳያል። የፋርስን ንጉስ እያገለገለ ሳለ በኢየሩሳሌም ላይ እየደረሰ ስለነበረው አሳዛኝ ችግር ወሬ ሰማ፤በዚህም ጊዜ በከተማይቱና በነዋሪዎቿ ላይ በሚደርሰው ችግር እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ወደ እርሱ አብዝቶ ማለደ ። ምዕ 2 ነህምያ የኢየሩሳሌም አገረ ገዥ ሆኖ እንዲላክ እግዚአብሔር ንጉስ አርጤክስስን እንዴት እንደ ተጠቀመበት እንዲሁም የነህምያን ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ያመለክታል። ከምዕ 3:1-7:1-73 ያለው ደግሞ ከከተማይቱ ውስጥና ከውጭ ከባድ ተቃውሞ ቢነሳም የፈራረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር በ 52 ቀናት እንደገና ለመሥራት ነህምያ የከተማውን ሕዝብ ለማስተባበር የነበረውን ድፍረት ፣ጥበብና የአመራር ሰጭነት ብቃት ይገልጻል።

**II. በዕዝራ መሪነት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ማነቃቃት:**

(**ከምዕ 8:1-10:39**): በዚህ ክፍል በካህኑ ዕዝራ መሪነት በኢየሩሳሌም ሕዝብ መካከል የተከናወነው መንፈሳዊ ተሐድሶ በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው።

**III. በነህምያ መሪነት በአገሪቱ ላይ አጠቃላይ ተሐድሶ ማምጣት:**

**(ከምዕ11:1-13:31) :**በነህምያ በኩል በመንፈሳዊ ተሐድሶው ወቅት የተከናወኑ ዐቢይ ብሔራዊ ጉዳዮች የእግዚአብሔር ሕግ ለሕዝቡ መነበቡ፣ለኃጢአት ንስሓ መግባትና ትሩፋኑ/ቅሬታዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለማስታወስና ለመጠበቅ የወሰዱት አዲሱ የውሳኔ አቋም ነበር ። ምዕራፍ 13 ነህምያ ዳግመኛ አገረ ገዥነት ተሹሞ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሰ ጊዜ ነህምያ ያካሄዳቸው የመጨረሻ የተሐድሶ እርምጃዎች የተጻፉበት ነው።

**ልዩ ገጽታ**

መጽሐፈ ነህምያን ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች፤**1)** በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ካለው የሽግግር ወቅት በፊት የነበረውን የመጨውረሻውን የአይሁድን የብሉይ ኪዳን ታሪክ ይገልጻል ፣ **2)** ነህምያና ነብዩ ሚልክያስ በአንድ ዘመን የነበሩ በመሆናቸው የነህምያ መጽሐፍ የመጨረሻውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ማለትም የትንቢተ ሚልክያስን ታሪካዊ ዳራ ያመለክታል ፣ **3)**ነህምያ በመንግሥት ሥራ ላለ መንፈሳዊ መሪ ያለነቀፋ በሐቀኝነት ፣ በማያወላውል እምነት ፣ ለተጨቆኑት በመራራት ፣ በአመራር አደረጃጀት ልዩ ተሰጥኦ የነበረው የሕዝብ አገልጋይ ነበር ፣ **4**) በብሉይ ኪዳን በላቀ ሁኔታ በመጸለይ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት መሪዎች አንዱ ነው ። ከዐሥራ አንድ ጊዜ ባላነሰ ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየ ወይም እንደማለደ ተዘግቧል ፣ **5)** መጽተሐፈ ነህምያ ሥዕላዊ በሆነ መንገድ እንደዚያ ዓይነቱ ጸሎት ፣ መሥዋዕትነት፣ብርቱ ሥራና ጥንካሬ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ራዕይ ለመፈጸም በአንድነት እንደሚያሳፈልጉ ገልጾአል።

**መልካም ጥናት!**

## ጥናት 1: የነህምያ ሃዘን እና ጸሎት
## <u>የምንባብ ክፍል: ነህ 1፤1-11</u>

**መግቢያ /Introduction/**: በዛሬው ጥናት ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ዜና ሰምቶ እጅግ ማዘኑን እና የፈረሰውንም ቅጥር መልሶ ለመስራት የወሰዳቸውን የመጀመሪያ እርምጃዎች እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

1. ነህምያ ወንድሙን ሃናኒያን ሲያገኝ ለማወቅ የፈለገው ነገር ምን ነበር? አስፈላጊነቱስ?
2. በቁ 4 ነህምያ ቅሬታዎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ ካወቀ በኋላ የተሰማውን ስሜት ግለጽ። የወሰደውስ እርምጃ ምን ነበር?
3. በቁ. 5 ነህምያ በጸሎቱ መግቢያ ላይ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ባህርይ የገለጸው ነገር ሊሰራ ካለው ስራ ጅማሬ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
4. (ከቁ. 6 – 9) የውድቀታቸውና የጥፋቱ ሃላፊነት የማን እንደሆነ ይናገራል? ለምን?
5. በቁ 11 ነህምያ ቅጥሩን ለመስራት የወሰደው እርምጃ ምንድን ነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application**

6. የእግዚአብሔርን ቤት ስራ ለመስራት እና አገራችንንም ለመርዳት ስለ ምንወስደው የመጀመሪያ እርምጃ ከነህምያ ሕይወት ምን ልንማር ይገባል?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ነህምያ ለራሱ በሚመቸው ምድራዊ ስፍራ የነበረ ቢሆንም የኢየሩሳሌምን ቅጥር መፍረስና የወገኖቹን ምድራዊ ኑሮ ጉስቁልና ሲሰማ ከልብ ሲያዝንና ስለ መፍትሄውም በእግዚአብሔር ፊት ለአያሌ ቀናቶች ሲጸልይ አይተናል። እኛም በሕይወታችን ስለ ቤተሰብ ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ አገራችን ብዙ ጉዳት ሁሌም እንሰማለን። ጌታ ስለ ወገኖቻችንና ስለ አገራችን ግድ የሚለው የነህምያ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ልብ ይስጠን። አሜን!

**ያሰላስሉ!Meditate**

**“ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፥” ነህ 1:*4***

## ጥናት 2: የነህምያ የፈረሰውን ቅጥር ጉብኝት
## <u>የምንባብ ክፍል: ነህ 2 ፤1-20</u>

**መግቢያ/ Introduction/:** ባለፈው ጥናት ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ዜና ሰምቶ እጅግ ማዘኑን እና የፈረሰውንም ቅጥር መልሶ ለመስራት በጸሎት እንደቆየና ሞገስን ከእግዚአብሔር እንደጠየቀ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ነህምያ ከንጉስ አርጤክስስ ፈቃድ ለማግኘት ሲጠይቅ እና ከተፈቀደለትም በኋላ የኢየሩሳሌምን ፍርስራሽ ቅጥር ሄዶ ሲጎበኝ እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች** /Discussion Questions/

1. (ከቁ1-3) ነህምያ የቅጥሩን ስራ ተግባር አስኪጀምር ድረስ ምን እያደረገ ቆየ?
2. ንጉሱ እድል በሰጠው ጊዜ ነህምያ የጠየቃቸው ነገሮች ምን ነበሩ?
3. ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣስ በኋላ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? (11-18)
4. በቁ.17 ለስራው አብረውት እንዲቆሙ ያነሳሳው እነ ማንን ነበር? አስፈላጊነቱስ?
5. ነህምያ ተቃዋሚዎቹን በምን ተደግፎ ሊቋቋም ቻለ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application**

6. እናንተስ በዚህ ወቅት ሸክም ሆኖባችሁ እየጸለያችሁበት ያለ ነገር አለ? ለጀመራችሁት መልካም ስራ/አገልግሎት/ ተቃዋሚ ሲመጣ መፍትሄው ምን እንደሆነ ተማራችሁ?

❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ነህምያ የቅጥሩን እድሳት ከመጀመሩ በፊት በአካል ከስፍራው ተገኝቶ ፍርስራሹን በማየት ገመገመ ። ከዚያም ለተሃድሶው ራሱን ብቻ ሳይሆን ወገኖቹንም በማሳተፍ ጀመረ። በጸሎት ቆይቶ ስለ ነበር ለተነሱበት ጠላቶቹ ሳይብረከረክ በውስጡ የተሞላውን የእግዚአብር ቃል በመግለጥ ለስራው የቆረጠ መሆኑን አሳየ። እኛም ዛሬ ብዙ የፈረሰ ቅጥር አለና በእግዚአብሔር ፊት ከጾምንና ከጸለይን በኋላ እንደ ነህምያ የፈረሰውን /የችግሩን ጥልቀት/ ተነስተን እንመልከት፣ወገኖችን እናስተባብር፣ የጠላትን ማላገጥ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል እናሸንፍ። ጌታ ይርዳን ። አሜን !

**ያሰላስሉ! / Meditate**

**"የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን፤" ነህ 2:*20***

## ጥናት 3: የቅጥሩ ሠራተኞች ስብስብ
## የምንባብ ክፍል: ነህ 3 ፤1-32

**መግቢያ /Introduction/:** ባለፈው ጥናት ነህምያ ከንጉስ በአርጠክስስ ፈቃድ ለማግኘት ሲጠይቅ እና ከተፈቀደለትም በኋላ የኢየሩሳሌምን ፍርስራሽ ቅጥር ሄዶ ሲጎበኝ እና አሁንም መሳለቂያ እንዳንሆን ተነስተን እንስራ በማለት ጥሪ ሲያቀርብ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የቅጥሩን በሮች እንዲሁም በስራው ላይ የተሳተፉ አገልጋዮች፣ ነገዶች፣ግለሰቦች ፣ቤተሰቦች፣ ነጋዴዎች ፣ባለሙያዎች እና ባለ ስልጣናት ዝርዝር እና በነህምያ አስተባባሪነት ሁሉም እስራኤላዊ በአንጻሩ ያለውን ቅጥር እንዳደሱ እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

1. በክፍሉ ላይ የተጠቀሱት የተለያዩ በሮች ስም ዘርዝሩ ። እነዚህ በሮች ልዩ ትርጉም ያላቸው ይመስልሃል/ሻል?
2. ቅጥሩ ሰፊ ፍርስራሹም ከባድ ቢሆንም ለመስራት ነህምያ የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበር?
3. የተለያዩ ነገዶች የተለያዩ በሮችን እንዲሰሩ ነህምያ የስራ ክፍፍል የመስጠቱ አስፈላጊነት ምን ይመስልሃል/ሻል?
4. በቁ. 3፣6፣13-15 ቁልፎችን መወርወሪያዎችን መሰራታቸውን በተደጋጋሚ ተጠቅሶ እናያለን ። ቅጥሮች ተሰርተው ቁልፎች ነገር ግን ባይደረጉላቸው ምን የሚመጣ ይመስልሃል/ሻል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application**

5. የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር ለመስራት ሁሉም በሚችለው አስተዋፅዖ ማበርከቱ በዚህ ዘመን ስለ እግዚአብሔር ቤት ወይም ለአገራችን ምን እንድናደርግ ያስተምረናል?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

በቅጥሩ በር ስራ ላይ በነህምያ አስተባባሪነት ሁሉም እስራኤላውያን ማለትም አገልጋዮች፣ ነገዶች፣ግለሰቦች ፣ቤተሰቦች፣ ነጋዴዎች ፣ባለሙያዎች እና ባለ ስልጣናትም ጭምር ሳይቀሩ ተሳትፈውበት እንዳደሱት ሁሉ ዛሬም በዚህ ዘመን በቤ ተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልጋዮች ፣ባለሙያዎች፣ነጋዴዎችና ባለስልጣናት ሁሉም ባለው ተሰጥኦ ቢሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ተሃድሶ የማይመጣበት ምክንያት እንዴት ሊኖር ይችላል ?

**ያሰላስሉ!Meditate**

**"ከማዕዘኑም መውጫ ጀምረው እስከ በጉ በር ድረስ ወርቅ አንጥረኞችና ነጋዴዎች አደሱ።"**
**ነህ 3:*32***

## ጥናት 4: በቅጥሩ ስራ ላይ ውጫዊ ተግዳሮት

**<u>የምንባብ ክፍል: ነህ 4 ፤1-23</u>**

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት የቅጥሩን በሮች እንዲሁም በስራው ላይ የተሳተፉ አገልጋዮች፣ ነገዶች፣ግለሰቦች ፣ቤተሰቦች፣ ነጋዴዎች ፣ባለሙያዎች እና ባለ ስልጣናት ዝርዝር እና በነህምያ አስተባባሪነት ሁሉም እስራኤላዊ በአንጻሩ ያለውን ቅጥር እንዳደሱ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጠላት ከውጭ ሆኖ ልዩ ልዩ ስልቶችን እየቀያየረ ነህምያንና ሕዝቡን እንዴት እንደተዋጋ እና የቅጥሩን ስራ ለማስተጓጎል እንደሞከረ በአንፃሩ ደግሞ የነህምያና የሕዝቡ ምላሽ ምን እንደነበረ እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

1. (ከቁ1-6) የቅጥሩ መሰራት በተሰማ ጊዜ ሰንበላጥና ጦብያ ስራውን ለማስተጓጎል የተጠቀሙበት የመጀመሪያ ስልት ምን ነበር ? የነህምያና የህዝቡ ምላሽስ ?
2. (ከቁ.7-9) የቅጥሩ መታደስ እየተፋጠነ እንደሄደ እነዚሁ ጠላቶች በሰሙ ጊዜ ስራውን ለማስተጓጎል የተጠቀሙበት አዲስ ስልት ምን ነበር? የነህምያና የህዝቡ ምላሽስ?
3. በቁ .10 ጠላት ነህምያንና ሕዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥ በተደጋጋሚ ሲዋጋ እናያለን ። ተስፋ መቁረጥን ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?
4. (ከቁ 10-14) ጠላቶች በቀየሱት የውጊያ ስልት ተስፋ የቆረጡትንና የፈሩትን የእስራኤል ልጆች ተስፋ ከመቁረጥና ከፍርሃት እንዲወጡ ነህምያ ምን አላቸው?
5. (ከቁ.16-23) የቅጥሩን ስራ ለማስኬድ ነህምያ የተጠቀመባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

6. በዚህ ዘመን እኛ የእግዚአብሔርን ስራ እንዳንሰራ ወይም አገራችንን እንዳንደግፍ ጠላት በምን ሊዋጋን ይችላል ? እኛስ እንደ ነህምያና እንደ እስራኤላውያን ምን ማድረግ አለብን?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ጠላት በነህምያ የቅጥር ስራ ላይ በንቀት በማላገጥ ፣ ተስፋ ለማስቆረጥ በማስፈራራት፣ በዚያም አልሳካ ሲለው ደግሞ በማታለል የተጀመረውን የእግዚአብሔር ስራ ለማስቆም ደጋግሞ ሲሞክር በአንጻሩ ግን የነህምያን እግዚአብሔር ላይ መደገፍና በጽናት ወደፊት መቀጠል ተመልክተናል ። የድሮው ሰይጣን ዘንድሮም ስልቱን ይቀይር ይሆን እንጂ የፈረሰውን ቅጥር ልንሰራ ስንነሳ እኛንም እንደ ነህምያ የሚዋጋን መሆኑ እርግጥ ነው። ነገር ግን ከጌታ ጸጋ የተነሳ ሊያሸንፈን ፈጽሞ እንደማይችል ተረድተን ጌታን ተማምነን የተሃድሶውን እንቅስቃሴ መቀጠል ይገባናል።

**ያሰላስሉ!Mediate**

**" ቅጥሩንም ሠራን፤ ቅጥሩም ሁሉ እስከ እኵሌታው ድረስ ተጋጠመ፤ የሕዝቡም ልብ ለሥራው ጨከነ ። "** **ነህ 4:*6***

## ጥናት 5: በቅጥሩ ሥራ ላይ ውስጣዊ ተግዳሮት

## የምንባብ ክፍል:ነህ 5፤1-19

**መግቢያ/Introduction/ :**ባለፈው ጥናት ጠላት ከውጭ ሆኖ ልዩ ልዩ ስልቶችን እየቀያየረ ነህምያንና ሕዝቡን እንዴት እንደተዋጋ እና የቅጥሩን ስራ ለማስተጓጎል እንደሞከረ በአንፃሩ ደግሞ የነህምያና የሕዝቡ ምላሽ ምን እንደነበረ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጠላት ስልቱን ቀይሮ ከንዘብ/ከሃብት ጋር በተያያዘራስ ወዳድነት የሆኑ ሰዎችን ከመሃል ማስነሳት በአይሁድ መካከል ከባድ የእርስ በርስ ግጭት መከሰቱንና ነህምያ ይህንን ብርቱ ውስጣዊ ችግር ለመፍታት የወሰደውን የመፍትሄ እርምጃ እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

1. (ከቁ. 1-5) የህዝቡ አቤቱታ ምን ነበር? ችግሩንስ የፈጠሩት እነማን ነበሩ?
2. (ከቁ.6-13) ነህምያ የህዝቡን ጩህት ሲሰማ እጅግ ከመቆጣት ባለፈ ችግሩን ለመፍታት የወሰዳቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ምን ነበሩ? የሕዝቡስ ምላሽ?
3. ነህምያ በይሁዳ አገረ ገዥ በነበረበት ዘመን ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ከቁ.14-18 የተጠቀሱትን የግሉን የሕይወት ንጽህና ምስክርነቶች በዝርዝር ተነጋገሩ።
4. ነህምያ ለሕዝቡ ስላደረገው መልካም ነገር ብድራትን ይለምን የነበረው ከማነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application**

5. ብዙ ገንዘብ ለማከማቸት ስትል/ዪ ወንድምና እህትን መጠቀሚያ ማድረግ እንደሌለብን በግል ሕይወትህ የተረዳኸውን/ሽውን ለቡድንህ/ሽ አካፍል/ዪ።

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ጠላት የእግዚአብሔርን ህዝብ ከውጭ ሆኖ መዋጋት ሲያቅተው በውስጥ ሆኖ በህዝቡ መካከል ልዩነቶችን ይፈጥራል ። ለዚህም ደግሞ አንዱና ትልቁ መሳሪያው ራስ ወዳድነት የሆኑ ሰዎችን ከመሃል ማስነሳት ነው ። ራስ ወዳድነት ማለት ራስን ወይም የራስን ፍላጎት ከማንም ወይም ከምንም በላይ ማስቀደም ማለት ነው። ይህን እውነት በማስተዋል ጠላት እድል ፈንታን ፈጽሞ እንዳያገኝ ልንጠነቀቅ ይገባል ።

**ያሰላስሉ!Meditate**

**"አምላኬ ሆይ፥ ለዚህ ሕዝብ ያደረግሁትን ሁሉ ለበጎነት አስብልኝ ።" ነህ 5:19**

## ጥናት 6: የቅጥሩ እድሳት መጠናቀቅ

## <u>የምንባብ ክፍል: ነህ 6፤1-19</u>

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት ጠላት ስልቱን ቀይሮ ከንዘብ/ከሃብት ጋር በተያያዘራስ ወዳድነት የሆኑ ሰዎችን ከመሃል ማስነሳት በአይሁድ መካከል ከባድ የእርስ በርስ ግጭት መከሰቱንና ነህምያ ይህንን ብርቱ ውስጣዊ ችግር ለመፍታት የወሰደውን የመፍትሄ እርምጃ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጠላት ሌሎች የረቀቁ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ለማስፈራራትና ተስፋ ለማስቆረጥ ቢሞክርም በእግዚአብሔር እርዳታና በነህምያ ጽናት የቅጥሩ ስራ ሙሉ በሙሉ በድል መጠናቀቁን እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

1. (ከቁ. 1-4) ጠላቶች ለነህምያ ለአራት ጊዜ የላኩለት መልዕክት ምን የሚል ነበር? የነህምያስ ምላሽ ምን ነበር?
2. የሰንበላጥ አምስተኛ ደብዳቤው መልዕክት ምን የሚል ነበር? የነህምያስ ምላሽ?
3. ነብዩ ሸማያ ከቤተ-መቅደስ ውስጥ እንዲሸሸ ሲጋብዘው ነህምያ ለምን እምቢ አለ?
4. (ከቁ. 17-19) ከእስራኤል ጠላቶች ጋር መልእክት ይለዋወጡ የነበሩት እነማን ነበሩ?
5. ከእስራኤል ጠላቶች ጋር ለዚህ አይነት ህብረት ያበቃቸው ሁኔታ ምን ነበር? ቁ 18.
6. (ከቁ.14-15) በዚህ ሁሉ ተቃውሞና ውጊያ ላይ ስራው እንዲፈጸም ነህምያንና ህዝቡን የረዳቸው ነገር ምን ይመስላችኋል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application**

7. ጠላት በዚህም ዘመን የውጊያ ስልቶችን እየቀያየረ በግል ሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በአገራችን ብዙ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ ይታወቃል ። ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ ጥቂቶቹን በመጥቀስ እኛስ እንደ ነህምያ ምን ማድረግ እንዳለብን በዝርዝር ተወያዩ።

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

የፈረሰው ቅጥር እንዳይሰራ ጠላት ስልቱን እየቀያየረ እንዴት እንደሚዋጋ በአንፃሩ ደግሞ የነህምያን ጽናት ተመልክተናል። እኛም የጠላት የውጊያ ስልት በየዘመኑ የተለያየ መሆኑን ተረድተን ተስፋ ሳንቆርጥ ለተጠራንበት አገልግሎት ህይወታችንን በመስጠት እግዚአብሔር የሰጠንን ተልዕኮ በታማኝነት እስከ ፍጻሜው ድረስ መወጣት ይገባናል ።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"እኔም ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፥ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም፤ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል? ብዬ መልእክተኞችን ላክሁባቸው። "ነህ 6:3**

## ጥናት 7: ቅጥሩን በንቃት መጠበቅ

## የምንባብ ክፍል: ነህ 7፤1-73

**መግቢያ/ Introduction/:** ባለፈው ጥናት ጠላት ሌሎች የረቀቁ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ለማስፈራራትና ተስፋ ለማስቆረጥ ቢሞክርም በእግዚአብሔር እርዳታና በነህምያ ጽናት የቅጥሩ ስራ ሙሉ በሙሉ በድል መጠናቀቁን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእግዚአብሔር ኃይልና እርዳታ የተሰራውን ስራ ጠላት እንደገና መጥቶ እንዳያበላሸው በንቃትና በትጋት ስለመጠበቅ እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች /Discussion Questions/**

**1**. (ከቁ 1- 2) የፈረሰው የኢየሩሳሌም ቅጥር ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ነህምያ ያከናወነው ተግባር ምን ነበር? ለምን?

**2**. ለዚህ ስራ በኢየሩሳሌም ላይ የተሾሙት ሰዎች እነማን ነበሩ? ስለ ሰዎቹ ብቃት ነህምያ ምን ማስረጃ ያቀርባል?

**3**. (ከቁ. 3 -4) ነህምያ ስለ ከተማይቱ ጥበቃ ምን ምን ትእዛዞችን አስተላለፈ?

**4**. በቁ. 5 ላይ ነህምያ እግዚአብሔር «በልቤ አደረገ» የሚለው ምንድን ነው?

**5**. (ከቁ.64-73) በዚህም ስራ በቀደምተኝነት የተሳተፉት እነማን ነበሩ? የትውልድ ሃረጋቸው ያልተገኙት ካህናት ላይ ምን ተወሰነባቸው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

6.በዚህ ዘመን እኛ አማኞች በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በንቃት መጠበቅ ያለብን ነገር ምን ይመስላችኋል?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

በብዙ የእግዚብሔር እርዳታ የተሰራውን ቅጥር ጠላት መልሶ እንዳያፈርሰው ነህምያ በትጋት እንዲጠበቅ እንዳስደረገው ሁሉ እኛም በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ያከናወነልንን ስራ በክርስቶስም ደም በነፃ ያገኘነውን ሕይወት በብዙ የጸሎት ትጋትና መንፈሳዊ ውጊያ ጽናት መጠበቅ ይገባናል ።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**“,,እነርሱም ቆመው ሳሉ ደጆቹን ይዝጉ፥ ይቈልፉም፤ ከኢየሩሳሌምም ሰዎች አንዳንዱን በየተራው አንዳንዱንም በየቤቱ አንጻር ጠባቆችን አስቀምጡ አልኋቸው።” ነህ 7:3**

## ጥናት 8: የሕጉ መጽሐፍ መነበብ
## የምንባብ ክፍል: ነህ 8፤ 1-18

**መግቢያ /Introduction/:** ባለፈው ጥናት በእግዚአብሔር ኃይልና እርዳታ የተሰራውን ስራ ጠላት እንደገና መጥቶ እንዳያበላሸው በንቃትንና በትጋት ስለመጠበቅ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእስራኤል ህዝብ እንደ አንድ ሰው በአንድ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት መቅረባቸው በሕይወታቸው ያመጣውን ለውጥ በማየት እኛም ሕያው ቃሉን አክብረን ብንታዘዘው ልናገኝ የምንችለው የሕይወት ለውጥ እንዳስሳለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/Discussion Questions/**

1. (ከቁ. 1-3) የእስራኤል ልጆች ከሚኖሩባቸው ከተሞች ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆኖ መሰብሰብ ለምን አስፈለጋቸው? ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ በውሃው በር ለተሰበሰበው ህዝብ በየቀኑ ለስንት ስዓታት ያህል አነበበ?
2. (ከቁ. 3-6) የህዝቡ በጥሞና መስማትና የሰጡት ምላሽ ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን አክብሮት ምን ያመለክታል?
3. (ከቁ. 7-8) ዕዝራና ሌሎች አገልጋዮች ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት እንዲረዱ ከማንበብ ባለፈ ያደረጉት ነገር ምን ነበር?
4. (ከቁ. 9-12) የተሰበሰበው ህዝብ ያለቅሱ የነበረው ለምንድን ነው? ነህምያ ፣ ዕዝራና ሌሎች አገልጋዮች ምን እንዲያደርጉ አደፋፈሯቸው?
5. በቁ.13 ላይ በሁለተኛው ቀን የእስራኤል ልጆች የተሰበሰቡት ምን ለማድረግ ነበር ?
6. (ከቁ. 14 -18) ከሙሴ የህግ መጽሐፍ ምን የተለየ ትዕዛዝና ስርዓት አገኙ? ይህ ስርዓት ለምን ያህል ጊዜ ተቋርጦ ነበር?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

7. የእስራኤል ህዝብ ለሕጉ ቃል ያላቸውን ጥማትና አክብሮት ስትመለከቱ ዛሬ ክርስቲያኖች ለቃሉ ያለንን ጥማትና አክብሮት እንዴት ትመዝኑታላችሁ? ምክንያቱ ምንድን ነው ትላላችሁ? ይህንን ለመለወጥ ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ ይጠበቅብናል?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ዛሬው ክፍል በዝርዝር እንደተመለከትነው በመሪነት ደረጃ የነበሩት ነህምያና ካህኑንና ጸሓፊው ዕዝራ፣አገልጋዮቹና የእስራኤል ህዝብ በአጠቃላይ እንደ አንድ ሰው ሆነው ቃሉን ያነቡ፣ ይሰሙ፣ይማሩና ይታዘዙም እንደነበረ ሁሉ በዚህ ዘመን የምንገኝ እኛም እንደ ቤተ ክርስቲያን ለቃሉ ትኩረት መስጠታችንን በተግባር በመታዘዝ ልናሳይ ይጠብቅብናል።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**“ከመጀመሪያውም ቀን ጀምሮ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ዕለት ዕለት የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ ያነብብ ነበር።” ነህ 8:18**

## ጥናት 9: ስለ በደል ጥልቅ ንስሓ
## የምንባብ ክፍል: ነህ 9፤1-15

**መግቢያ/ Introduction /:** ባለፈው ጥናት የእስራኤል ህዝብ እንደ አንድ ሰው በአንድ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት መቅረባቸው በሕይወታቸው ያመጣውን ለውጥ በማየት እኛም ሕያው ቃሉን አክብረን ብንታዘዘው ልናገኝ የምንችለው የሕይወት ለውጥ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእስራኤል ህዝብ የገቡትን ጥልቅ ንስሓና እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ለእስራኤል ያደረገውን መልካምነት በዝርዝር እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

**1**. (ከቁ.1-6) የእስራኤል ልጆች ከአምላካቸው ጋር የነበራቸውን የቀድሞውን ህብረት ለማደስ ንስሓ የገቡበትን ሁኔታ በዝርዝር ጥቀሱ ።

**2.** (ከቁ.7-15) እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ/ለእስራኤል ያደረገውን በዝርዝር አስቀምጡ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

**3**. እግዚአብሔር ለህዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን በየዘመናቱ እየፈጸመ ሲረዳቸው ፤ዛሬ በእኛ ሕይወት ውስጥ ያደረገውን ከእኛም ዘንድ የሚጠበቀውን አብራራ?

**4**. በአጠቃላይ በአሁኑ ዘመን ላለን ክርስቲያኖች ይህ ጥናት ምን መልእክት አለው?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

የእስራኤል ህዝብ ራሳቸውን በፍጹም አዋርደው ቃሉን በማንበብ እግዚአብሔርን እያመለኩ እርሱም በምሕረቱና በመልካነቱ ሁሉ እንደተገለጠላቸው ሁሉ፤ እኛም እንደ እስራኤል ሕዝብ በእውነተኛ ንስሓ ሕይወት ራሳችንን አንጽተን ፊቱን ብንፈልግ እንደ ቃል ኪዳኑ መልካምነቱ ለህዝባችንም በግል ሕይወታችን ተገልጦ ማየት ይሆንልናል።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**“የእስራኤልም ዘር ከእንግዶች ሁሉ ራሳቸውን ለዩ፥ ቆመውም ኃጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን ኃጢአት ተናዘዙ ።” ነህ 9:2**

## ጥናት 10: የእግዚአብሔር ምሕረት ባለጠግነት
## የምንባብ ክፍል: ነህ 9 ፣16-38

**መግቢያ:** ባለፈው ጥናት የእስራኤል ህዝብ የገቡትን ጥልቅ ንስሓና እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ለእስራኤል ያደረገውን መልካምነት ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ በደልና በአንፃሩ ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገላቸውን ምሕረትና መልካምነት ከማየታቸው የተነሳ እግዚአብሔርን ዳግም ላለመበደል “ስለዚህም ሁሉ የታመነውን ቃል ኪዳን አድርገን እንጽፋለን፤ አለቆቻችንም ሌዋውያኖቻችንም ካህናቶቻችንም ያትሙበታል” ብለው ቃል መግባታቸውን እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

**1**. (ከቁ 16-17) የእስራኤል ህዝብና አባቶች እግዚአብሔርን ያሳዘኑት በምን ነበር?
**2.** (ከቁ. 18-25) እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገውን የምሕረቱን መገለጫዎች በመዘርዘር ተነጋገሩ ።
**3**. በቁ. 26 የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን በመዘንጋት ምን አደረጉ? ምንስ አስከተለባቸው?
**4**. (ከቁ.27-31) የእስራአልን ሕዝብ በደልና በአንፃሩ ደግሞ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ምሕረት በመዘርዘር ተወያዩ ፡፡
**5**. (ከቁ. 32-37) ሌዋውያኑ ለእግዚአብሔር ያቀረቡት ልመና ምን ነበር?
**6.** በቁ. 38 ላይ የእስራኤል ህዝብና መሪዎች ምን ለማደረግ ቃል ገቡ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

**7.** እግዚአብሔር እንደገባው ቃል ኪዳን ለእስራኤል የጠላቶቻቸውን ምድር ማውረሱን ስትመለከቱ ዛሬ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ የወረሰነው ምንድን ነው?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደተናገረው ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅና የሚያደርግ አምላክ መሆኑንና የእስራኤል ህዝብ ያሳየውን መልካምነት በስፋት ዳሰናል ። የእስራኤል ህዝብም ይህንን ምሕረቱን በማሰብ ላለመበደል ቃል ሲገቡ ተመልክተናል ። ዛሬም እኛም በደላችን ብዙ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያሳየንን ምሕረት በማሰብ እርሱን በሕይወታችን እንዳንበድል ቃል ልንገባና በጸጋው በመደገፍ በቃል ኪዳናችን ልንጸና ይጠበቅብናል። ።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

***“ነገር ግን አንተ ቸርና መሐሪ አምላክ ነህና በምሕረትህ ብዛት ፈጽመህ አላጠፋሃቸውም፥ አልተውሃቸውምም።” ነህ 9:31***

## ጥናት 11: እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የተደረገ ውል
## የምንባብ ክፍል ፡ ነህ 10 ፤1-39

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት የእስራኤልን ሕዝብ በደልና በአንፃሩ ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገላቸውን ምሕረትና መልካምነት ከማየታቸው የተነሳ እግዚአብሔርን ዳግም ላለመበደል "ስለዚህም ሁሉ የታመነውን ቃል ኪዳን አድርገን እንጽፋለን፤ አለቆቻችንም ሌዋውያኖቻችንም ካህናቶቻችንም ያትሙበታል " ብለው ቃል መግባታቸውን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእስራአል ሕዝብ ከክፉ መንገዳቸው ስለ መመለሳቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ፍርዱንም ሥርዓቱንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ ቃል በመግባት ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ በውል ስምምነት /ቃል ኪዳን ሰነድ/ ላይ ስማቸውን ያተሙትን ወገኖች ዝርዝር እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

**1**. (ከቁ 1 – 27) በተዘገበው ታሪክ ህዝቡ ያደረገው ነገር ምን እንደሆነና የድርጊቱንም አስፈላጊነት በዝርዝር ተወያዩበት ።

**2**. (ከቁ 29 – 31) ባለው ክፍል ሊያደርጉት ቃል የገቡትን ነገሮች ዘርዝሩ ። ይሄ በዕለት ተዕለት እንዴት ሊገለጥ ይችላል ?

**3**. በቁ 35 – 37 በኲራትን ለእግዚአብሔር ማቅረባቸው አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?

**4**. ከቁ 38 – 39 ህዝቡ ከዚህ በኋላ ምን ዓይነት የሕይወት ለውጥ ለማድረግ ወሰኑ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

**5**. ዛሬስ በየዕለት ኑሮህ/ሽ ከእግዚአብሔር ጋር የጸና ኅብረት እንዲኖርህ/ሽ ማድረግ ያለብህ/ሽ ነገሮች ምንድን ናቸው?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

እግዚአብሔር አምላካችንና አባታችንም ስለሆነ በማንኛውም የሕይወትና የኑሮ ዘርፍ (ቤተሰብ ፤ ቤተ ክርስቲያን፤ ስራ) በነገር ሁሉ ጌታን ልናከብረውና ልናስቀድመው ይገባል ፡፡

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"በእግዚአብሔርም ባሪያ በሙሴ እጅ በተሰጠው በእግዚአብሔር ሕግ ይሄዱ ዘንድ፥ የጌታችንንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ፍርዱንም ሥርዓቱንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ እርግማንና መሐላውን አደረጉ "። ነህ 10:29**

## ጥናት 12: አዲሶቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
## የምንባብ ክፍል ፡ ነህ 11 ፤1-36

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት የእስራኤል ሕዝብ ከክፉ መንገዳቸው ስለ መመለሳቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ፍርዱንም ሥርዓቱንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ ቃል በመግባት ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ በውል ስምምነት /ቃል ኪዳን ሰነድ/ ላይ ስማቸውን ያተሙትን ወገኖች ዝርዝር ተመልከተን ነበር። በዛሬ ጥናታችን ደግሞ ቅጥሩ ከተጠናቀቀ በኋላ በኢየሩሳሌም ለመቀመጥ የወሰኑትን የእስራኤልን ዘሮች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስና የተመለሱትም ተግባራዊ በሆነ መልኩ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት ቅጥሩን ከመጠበቅ ጀምሮ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዴት እንደተሳተፉ እንዳስሳለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

1. የህዝቡ መሪዎች በየትኛው ከተማ ተቀመጡ /ነዋሪ ሆኑ/? የቀሩት ሕዝብስ?
2. ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱትን ሰዎች በምን መንገድ ወሰኑ?
3. አብዛኞቹ /ዘጠና በመቶው/ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ያስቸገራቸው ነገር ያለ ይመስልሃል/ሻል?
4. በኢየሩሳሌም የተቀመጡት ዘሮችና አገልግሎቶች ቁጥራቸውስ ምን ያህል ነበር?
5. እንደዚህ በዝርዝር መጠቀሳቸው አስፈላጊነት ምን ይመስልሃል/ሻል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

6. እኛስ ዛሬ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የመጠበቅና የማገልገል ኃላፊነት ካለብን በምን እያገለገልክ/ሽ እንደሆነ ካልጀመርክም/ሽም ከዛሬ ጀምሮ በምን ለማገልገል እንደወሰንክ/ሽ ለቡድንህ/ሽ አካፍል/ ዪ።

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

እስራኤላውያን ቅጥሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ቅጥሩን ከመጠበቅ ጀምሮ በልዩ ልዩ መንገድ እግዚአብሔርን እንዳገለገሉት ሁሉ እኛም ይህንን እውነት በመረዳት በተሰጠን ጸጋ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ወስነን በፈቃደኝነት ራሳችንን ለጌታ መስጠት እንዳለብን ክፍሉ ያስተምረናል ።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"ሕዝቡም በፈቃዳቸው በኢየሩሳሌም ለመቀመጥ የወደዱትን ሰዎች ሁሉ ባረኩ ። "**

**ነህ 11:2**

## ጥናት 13: ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ካህናትና ሌዋውያን

## የምንባብ ክፍል ፡ ነህ 12 ፤1-26

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት ቅጥሩ ከተጠናቀቀ በኋላ በኢየሩሳሌም ለመቀመጥ የወሰኑትን የእስራኤልን ዘሮች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስና የተመለሱትንም ተግባራዊ በሆነ መልኩ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት ቅጥሩን ከመጠበቅ ጀምሮ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዴት እንደተሳተፉ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን ካህናትና ሌዋውያን ዝርዝር እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

1. (ከቁ 1 – 7) ከዘሩባቤልና ከኢያሱ ጋር የተመለሱት ካህናትና ሌዋውያን ቁጥራቸው ስንት ነው? ስልጣናቸውስ ምን ነበር?
2. (ከቁ 8 – 9) በመዘምራን ላይ የነበረ <u>መታንያ</u> ሲል ምን ማለቱ ነው? በየሰሞናቸው በአንጻራቸው ነበሩ ማለትስ?
3. (ከቁ 10 – 21) የኢያሱ ትውልድ እንዲሁም የካህናት ቤተሰብ አለቆች የነበሩትን ዘርዝር።
4. በቁ.24 የሌዋውያኑ አለቆችና ኢያሱ እግዚአብሔርን ያከብሩና ያመሰግኑ የነበሩት ማን በሰጣቸው መመሪያ መሰረት ነበር?
5. (ከቁ 25 - 26) በቅጥሩ በሮች አጠገብ የነበሩትን ዕቃ ቤቶች ለመጠበቅ በረኞች የነበሩት እነማን ነበሩ? የነህምያና የዕዝራ ኃላፊነትስ ምን ነበር?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

6. ቅጥሩ ከተጠናቀቀ በኋላ በተለያየ ኃላፊነት የሚመደቡ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጡ መደረጉ በዚህም ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን የሚሰራ የጌታ ሥራ ያለ መሆኑን ምን ያህል ተረድሃተል/ሻል?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ቅጥሩ ከተጠናቀቀ በኋላ በርካታ አገልግሎቶች የነበሩ በመሆኑ በተለያየ ኃላፊነት የሚመደቡ ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጡ መደረጉንና መመዝገባቸውን የተመለከትን ሲሆን ሁሉም ደግሞ ለቅጥሩ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር ጭምር እንደዋሉ ነው።ይህ የሚያመለክተን በእግዚአብሔር ቤት ምን ጊዜም ቢሆን የሚሰራ የጌታ ሥራ ያለ መሆኑን ተረድተን በተሰማራንበት ስፍራ መቆም እንዳለብን ነው።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"... እንደ እግዚአብሔር ሰው እንደ ዳዊት ትእዛዝ በየሰሞናቸው በወንድሞቻቸው ፊት ለፊት ያከብሩና ያመሰግኑ ነበር። "ነህ 12:24**

## ጥናት 14: የቅጥሩ ምረቃ በዓል

## የምንባብ ክፍል ፡ ነህ 12 ፣27-47

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን ካህናትና ሌዋውያን ዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ምረቃ በዓልና በምርቃቱም ፕሮግራም ላይ የእስራኤል ህዝብ (ቀድሞ የነበሩትንና አዲስ የመጡትን አገልጋዮች ሴቶችና ህጻናትን ጨምሮ) የቅጥሩን ስራ በድል እንዲያጠናቅቁ የረዳቸውን እግዚአብሔርን ታላቅ መስዋዕት በማቅረብ ማክበራቸውንና ከሩቅ እስኪሰማ ድረስ ደስታቸውን መግለፃቸውን እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

1. (ከቁ. 27 - 29) ሌዋውያኑን ከሚኖሩበት ስፍራ ፈልገው ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡአቸው ለምን ዓላማ ነበር?
2. በቁ. 30 ካህናቱና ሌዋውያኑ ለአገልግሎት ከመሰለፋቸው በፊት ያደረጉት ቅድመ ዝግጅት ምን ነበር?
3. የእግዚአብሔርን ሰው የዳዊትን የዜማ ዕቃ ይዘው የሚሄዱትን የመዘምራኑን ሰልፍ ይመራ የነበረው ማን ነበር?
4. በቁ. 43 በቅጥሩ መጠናቀቅ በእግዚአብሔር ስራ እጅግ የተደሰተው የኢየሩሳሌምም ህዝብ ደስታ እስከ የት ድረስ ሊሰማ ቻለ ?
5. (ከቁ 43 - 47) የእስራኤል ህዝብ ከደስታቸው የተነሳ በምርቃቱ ዕለት ለእግዚአብሔር ብዙ መስዋዕት ካቀረቡ በኋላ ሌላ ምን ምን እንዳደረጉ ዘርዝሩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

6. በእግዚአብሔር ፈቃድ የጀመራችሁትና ያቀዳችሁት ነገር ወደ መደምደሚያ ሲመጣ አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ወይስ ስለበፊቱ ምንም ሳናመሰግን አዲስ የልመና ጥያቄ ነው የምናቀርብለት?

- **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

እግዚአብሔር የሚያስጀምር ብቻ ሳይሆን የሚያስጨርስም አምላክ እንደሆነ ተረድተን እርሱ በሚሰጠን ድል መደስት ፣ክብሩን መልሶ ክብር ለሚገባው ለእርሱ ማቅረብ፣ አገልጋዮችን በተግባር መደገፍ ይጠበቅብናል ።

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"እግዚአብሔርም በታላቅ ደስታ ደስ አሰኝቶአቸዋልና በዚያ ቀን ትልቅ መሥዋዕት አቀረቡ፥ ደስም አላቸው፤ ሴቶቹና ልጆቹም ደግሞ ደስ አላቸው፤ የኢየሩሳሌምም ደስታ ከሩቅ ተሰማ ። "**

**ነህ 12:43**

## ጥናት 15: የመጨረሻው የነህምያ የተሐድሶ እርምጃ

## <u>የምንባብ ክፍል ፡ ነህ 13 ፤1-31</u>

**መግቢያ/Introduction/:** ባለፈው ጥናት የኢየሩሳሌምን ቅጥር ምረቃ በዓልና በምርቃቱም ፕሮግራም ላይ የእስራኤል ህዝብ (ቀድሞ የነበሩትን አሁን የመጡትን አገልጋዮች ሴቶችና ህጻናትን ጨምሮ) የቅጥሩን ስራ በድል እንዲያጠናቅቁ የረዳቸውን እግዚአብሔርን ታላቅ መስዋዕት በማቅረብ ማክበራቸውንና ከሩቅ እስኪሰማ ድረስ ደስታቸውንም መግለፃቸውን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ነህምያ የወሰደውን የመጨረሻውን የተሐድሶ እርምጃ በዝርዝር ከዳሰስን በኋላ እግዚአብሔር ለእኛም እንድናድሰው በግል በሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያናችንና በአገራችን የሰጠንን ወይም የሚሰጠንን የቅጥር ስራ ለማስቀጠል የሚያዘጋጀን ይህ የነህምያ መጽሐፍ ጥናት የድል ፍፃሜውን ያገኛል ።

**የመወያያ ጥያቄዎች/ Discussion Questions /**

**1.** (ከቁ.1 – 3) ህዝቡ የሕጉን መጽሐፍ ሲያነቡ ከሙሴ ሕግ ስለ ሞዓብ ልጆች ምን ተማሩ?

**2.**(ከቁ 4 –9) ኤሊያሴብ ለጦቢያ ያደረገው ነገር ክፉ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? ነህምያስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ኤልያሴብ ያደረገውን ባወቀ ጊዜ ምን እርምጃ ወሰደ?

**3**. (ከቁ 10 –22) ነህምያ ባልነበረበት ወቅት ተበላሽተው የጠበቁትን ነገሮችና ለማስተካከል የወሰዳቸውን እያንዳንቸውን የተሃድሦ እርምጃዎች በዝርዝር ተነጋገሩ ።

**4**. (ከቁ 23–30) አይሁድ ከሞዓባውያን ጋር የፈጠሩት የጋብቻ ግንኙነት ለምን እንደ ችግር ተቆጠረ?

**5.** እስራኤላውያን በዚህ ጉዳይ ተሃድሦ እንዲያደርጉ ነህምያ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ዘርዝሩ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ/Application/**

**6**. በዚህ ዘመን በግለሰብ በቤተ ክርስቲያንና በአገር ደረጃ የእውነተኛ ተሃድሶ እዳይመጣ ዋን ዋና እንቅፋቶቹ ምን ይመስሉሃል/ሻል? አንተስ/ቺሽ የመፍትሄው አካል ለመሆን እንደ ነህምያ በግለሰብ ደረጃ ምን ለማድረግ ወስነሃል/ሻል?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ ያልተዳሰሰ መሰረታዊ አሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ ።**

**ማጠቃለያ/Summary/**

ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መፍረስና የወገኖቹን ምድራዊ ኑሮ ጉስቁልና ሲሰማ ከማዘንና ከመጸለይ አልፎ ለራሱ የሚመቸውን ምድራዊ ስፍራ ለቆ ሄዶ የፈረሰውን ቅጥር ሲያድስ ፤እርስ በርስ ሲጣሉበት ሲያስታርቃቸው፣ድሆችን ሲረዳ፣ ከመንግስታት ጋር ሲጋፈጥላቸው ፤ጠላቶቻቸውን ሲቋቋምላቸው፣እግዚአብሔርን ሲበድሉ ንስሓ ሲገባላቸው፣ በፍቅር ሲገስጻቸው፣አደራ ብሎ ቃል ሲያስገባቸው ፤በመጽሐፉ አስራ ሦስት ምዕራፎች ዳሰናል ። በአጠቃላይ ነህምያን እግዚአብሔር የሞላበት የፍቅር ሸክም ኢየሩሳሌምና ወገኖቹ አይሁድ መቼም ሁሌም እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በልቡ ውስጥ ነበሩ ቢባል ማጋነን አይሆንም ። የተሃድሶ ተልዕኮውን እንዲያጠናቅቅ ጌታ ድል አቀዳጅቶታል ። እኛም በሕይወታችን ስለ ቤተሰብ ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ አገራችን እግዚአብሔር የሰጠንን የፍቅር ሸክም በድል እንድንፈጽመው ጌታ ይርዳን። አሜን!

**ያሰላስሉ!Meditate!**

**"ሕጉንም በሰሙ ጊዜ ድብልቁን ሕዝብ ሁሉ ከእስራኤል ለዩ ።" ነህ 13:3**